# የባሕር-በር ጥያቄ ከኢትዮጵያ አንድነት፣ የሕዝብ ሉዓላዊነት፣ ከፀጥታ፣ ከልማትና እድገት ዋስትናነት አኳያ፤

*የግል አስተያየት፦- የግል አስተያየት - ኢያል ሰው ደሴ - ክፍል ሦስት*

ምናልባት ከጥቂቶች በስተቀር ኢትዮጵያውያን አገራቸው በባለቤትነት የምትቆጣጠረው የባሕር በር እንደሚያስፈልጋት ይስማማሉ ማለት እችላለሁ:: ሆኖም የባሕር ጠረፍ ወይም የባሕር በር ጥያቄን በሚመለከት አንድ-ወጥ አመለካከት እንደሌለን ይታወቃል:: ቀደም-ሲል ለመጠቆም እንደሞከርኩት ጥያቄውን አወዛጋቢና ከላይ ሲታይ አስቸጋሪ ሆኖ እንዲገኝ ያደረገው ደግሞ ሌላ ሣይሆን በተለይ የቀይ ባሕር ጠረፍ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ አገራዊ የመንግሥት ሥልጣን በጨበጠው ሕወሓት መሪዎች ቀጥተኛ አስተናባሪነትና ድጋፍ "ነፃነቷን" ባወጀችና ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ባለች ኤርትራ ሥር መሆኑ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ መንግሥት ስም ያለው ድርጅት (የሕወሓት/ኢሕአዴግ) መሪዎች ጉዳዩን በሁለቱም በኩል ያለውን ሕዝብ የሚጠቅም መፍትኄ ለመሻት ቀርቶ ዞር ብለው ለማስተናገድም እንኳ ጨርሶ ፍላጎት የሌላቸውና ሕዝቡ ተለያይቶ እንዲኖር ከሸዓብያ ያልተናነሰ ቁርጠኝነት ያላቸው በመሆኑ ነው ማለት ይቻላል::

ኢትዮጵያውያን መቸም ቢሆን ጥያቄውን ከማንሣት ወደ-ኋላ የማይሉት ደግሞ ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትለይ የተደረገበት ሂደት ኢ-ፍትኃዊና ፍርደ-ገምድል መሆኑና ኤርትራም ሸዓብያን በመሰለ ፀረ-ኢትዮጵያ ቡድን ሥር በመሆኗ ብቻ ሣይሆን ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ጠረፍ ላይ የሚኖራት የባለቤትነት መብት መነፈግ ከሚያስከትለው ዘርፈ-ብዙ ጠንቅ እንዲሁም መሠረታዊ ከሆነ ብሔራዊ ክብርና ጥቅም አኳያ ነው:: በተጨማሪም እያደገ ከሚሄደው ሕዝቧና ወገን ከሆነው የኤርትራ ሕዝብ ዘለቄታዊ ጥቅም፣ እንዲሁም ጉዳዩ በጥሞና ተመርምሮ ከወዲሁ ሰላማዊ መፍትኄ እንዲገኝለት ካልተደረገ ያላስፈላጊ ሆኖም ግን አይቀሬ ግጭትን የሚፈጥር ከመሆኑ አንፃር የምር ሊታይ ስለሚገባ ነው::

*"አንዴ ሄደዋልና በኤርትራ በኩል ያለውን የባሕር በር ጉዳይ እንርሣው"* የሚል አስተሣሰብ ያላቸው አንዳንድ ወገኖች የመኖራቸውን ያኽል፣ ቁጥራቸው በቀላሉ የማይገመት ኢትዮጵያውያን ደግሞ ለኤርትራ ሕዝብ ባላቸው ወገናዊ ስሜትና የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የኤርትራ ሕዝብ ተመልሶ አብሮ መኖሩ የማይቀር ነው ከሚል የጠና እምነት በመነሣት ይኽ አሁን በሸዓብያ ሥር የሚገኝ የባሕር ጠረፍ/በር በሌላ ከውጭ በመጣ ባዕድ ቁጥጥር ሥር እስካልሆነ ድረስ ጊዜ ይፈታዋልና መታገስ ይሻላል የሚል አመለካከት እንዳላቸው ይታወቃል::

የሆኖ ሆኖ ይኽን ዓቢይ ጉዳይ ከአገር ብሔራዊ ክብርና ጥቅም፣ ከአስተማማኝ ሰላምና ፀጥታ፣ ከደኅንነት፣ ከኀልውናና ከሕዝብ ሉዓላዊነት አኳያ ማየት ካልተቻለ ሌላው ቀርቶ ለማስተናገድ እንኳን ድፍረቱ እንደማይኖር፣ የወደፊት አደጋንም ለማስወገድ እንደማይቻል ግልጥ ነው:: እነዚኽ እሴቶች ደግሞ በቸልተኝነትም ሆነ በበጎ ምኞት ብቻ የሚረጋገጡ አይደሉም:: እንደሚታወቀው የአንድን አገር ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅ የሚቻለው ብሔራዊ ስሜትን የተላበሱ፣ ለሕዝብ ስሜትና ይሁንታ ተገዥ የሆኑ፣ ለአገር ታሪክ ከበሬታ፣ ለሕዝብም በጎ ራዕይና ገደብ-የለሽ ፍቅር ያላቸው፣ ከግል፣ ከቡድንና ከጎጠኝነት በላይ አገርንና ሕዝብን የሚያስቀድሙ መሪዎች ሲኖሩ ነው::

በእርግጥ የባሕር ጠረፍ/በር ጉዳይ ከላይ ሲታይ በመጠኑ የተወሣሰበ መሆኑና ቀላልና በሁለቱም በኩል "ሕጋዊ" ጥያቄዎችን አያስከትልም ማለት እንዳልሆነ ግልጥ ነው:: ይሁንናም የየትኛው ሕጋዊ መንገድ ማስኬድ አለ-ማስኬዱ የሚለካውና የሚታወቀው ግን መጀመሪያውኑ ጉዳዩ በግልጥ ሲነሣና ይፋ ውይይት እንዲደረግበት ድፍረቱ ሲኖር ይመስለኛል:: ድፍን-ድፍንፍን ባለ ሁኔታና ጥያቄው እንዳይነሣ በማፈን ወይም እርባናቸው በግልጥ ያልተፈተሹ አጓጉል ማስፈራሪያዎችን አስቀድሞ በመደንቀር ለጉዳዩ የሰከነ መፍትኄ ማስገኘት ደግሞ አይቻልም::

"ሁሉም ዝም መፀሐፉም ዝም" ዓይነት አካሄድ አንድም አምባ-ገነኖቹ የጥያቄውን መነሣት ከሥልጣናቸው ጋር በቀጥታ በማያያዝ ለአደጋ ያጋልጠናል ብለው ስለሚያስቡ

ጨርሶ እንዳይነሣ ያላቸውን ፍላጎት የሚያጠናክርላቸው ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ይኸ ተጻፍኖ እንዲቀር የሚፈልጉት ጉዳይ ይነሣል የሚል የውስጥ ስጋታቸውን ለማስወገድ ሲሉ በየጊዜው አዝማሚያዎችን በተወላገደ መልክ በማቅረብ አዲስ ዙር ውጥረት እንዲፈጠር፣ ጉዳዩ ስበት እንዳያገኝ አስቀድሞ ያልሆነ አጉል ስም በመስጠት ለማጨናገፍ መተናኮላቸውና ሌሎች የአፈና ተግባሮችን ለመፈጸምም በሰበብነት ሊጠቀሙበት እንደሚከጅሉ፣ ጥረትም እንደሚያደርጉ መገመቱ ከባድ አይሆንም፡፡

በጉዳዩ ላይ ከሚሰጡ በርካታ አስተያየቶች እንደምረዳው ብዙ ወገኖች የባሕር ጠረፍ (በር) እና የወደብ ጥያቄን በጥቅሉ አንድ እና ተመሣሣይ አድርገው ይመለከቱታል፡፡ ማንኛውም ወደብ በባሕር በርነት ሊያገለግል መቻሉ አጠያያቂ ባይሆንም በዚኸ ላይ ብቻ ማተኮሩ ግን የባሕር ጠረፍ (በር) ጥያቄን የተፈላጊነት ዓይነታ ጎን ውሱን ከማድረጉም በላይ ሕዝባዊ ገፅታውንና ብሔራዊ ባኅሪውን እንደሚያድበሰብሰው ግልጥ መሆን ያለበት ይመስለኛል፡፡

በበኩሌ ለምሣሌ ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ጠረፎች ላይ ሊኖራት ይገባል የምለውን የባለቤትነት ጥያቄ ሳነሣ የአፋርን ሕዝብ አንድነትና የኢትዮጵያዊነት መብት መከበርን ስሌቱ ባደረገ፣ ቢያንስ የወደብ ጠቀሜታን ለማረጋገጥ ሲባል ብቻ የኑዋሪውን ሕዝብ ማንነትና መብት መስዋዕት ባላደረገ፣ የሕዝብን ይሁንታና ዘለቄታዊ ትሥሥር ቁጥር ውስጥ ባስገባና መሠረታዊ የጋራ ጥቅምን አሣልፎ ባልሰጠ ሁኔታ ማለቴ ነው፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ የባሕር በር የባለቤትነት ጥያቄ ሲነሣ የኤርትራን ሕዝብ መብት በሚፃረርና መሠረታዊ ጥቅሙም በሚጎዳበት መልክ ሣይሆን እንዲያውም ጉዳዩን ለሠፊው የኤርትራ ሕዝብ አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋትን በሚሰጥ፣ የኤኮኖሚ እድገትና ፀጥታውን የመሣሰሉ ዘለቄታዊ ጥቅሞቹን የበለጠ የሚያጠናክር፣ የሚያረጋግጥና የሚያስጠብቅ ከመሆኑ አኳያ ነው፡፡

አዎን አንዳንድ ወገኖች ይኸንን አስተሣሰብ በደፈናው ውድቅ ለማድረግ *“አንተን በኤርትራ ጉዳይ ማን ወሣኝ አደረገህ”* ሊሉ እንደሚችሉ እገምታለሁ፡፡ እኔ ግን ጉዳዩን የማየው ከኤርትራ ጋር ቀጥተኛ የቤተሰብ ትሥሥር እንዳለው ሰው ብቻ ሣይሆን የኤርትራን ሕዝብ ዘለቄታዊ ጥቅም ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ውጭ አድርጎ እንደማያይ አንድ ኢትዮጵያዊ፣ የባሕር በር እጦት ባለፉ ትውልዶች ሰላም፣ መረጋጋት፣ እድገትና በአገራቸው አንድነት ላይ የደረሰው ፍዳና መከራ በነገዋ ኢትዮጵያ በሚኖሩ የወደፊት ትውልዶች ላይ እንዳይደርስ ካለኝ ምኞትና ፍላጎት፣ አልፎም ከአካባቢው ሰላምና መረጋጋት አኳያ መሆኑ ግልጥ ይሁንልኝ፡፡

በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ወገኖች ኢትዮጵያ ከኤርትራ ወንድምና እህቶቻችን ጋር በመስማማት ኤርትራ ውስጥ ያሉ ወደቦችን በተለይም አሰብን መጠቀም ይቻላል የሚል አሣብ ይሰነዝራሉ፡፡ እነዚኸ ወገኖች በአሁኑ ጊዜ *“ከኤርትራ ወንድምና እህቶቻችን ጋር በመስማማት”* ሲሉ በአቶ ኢሣኢያስ አፈወርቂ ከሚመራው የሸዓብያ መንግሥት ጋር ማለታቸው እንደሆነ ግልጥ ነው፡፡ ያ አስተሣሰብ ግን ከአቶ ኢሣኢያስና ከድርጅታቸው ተፈጥሮ ባኅሪ አኳያ ሲታይ የትም እንደማያደርስ ከወዲኹ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የወደብና የባሕር ጠረፍ (በር) ሲነሣ በአሁኑ ጊዜ እራሷን በቻለች ኤርትራ ባለቤትነት ሥር የሚገኙ ይዞታዎችን የሚመለከት ስለሚሆን ለሃያ ዓመታት ከኢትዮጵያ ቁጥጥር ውጭ በሆነ ጉዳይ ላይ ተመልሶ “የይገባኛል” ጥያቄ ማንሣቱ “አግባብነትም ሆነ ሕጋዊነት የለውም”፣ አልፈውም “አንዴ ፈልገው ሄደዋልና ልንረሣው ይገባል” የሚሉ ወገኖች ቁጥራቸው የሚናቅ አይደለም፡፡ ይሁንናም አንደኛ ቢያንስ ሁኔታዎች አሁን ባሉበት ደረጃ በጉልበት ወረራ ይካሄድ የሚል ያለ አይመስለኝም፡፡ ሁለተኛ የእነዚኸ ወገኖች አስተሣሰብ የባሕር ጠረፍ/በር ለአገር ኅልውናና አጠቃላይ ፀጥታ ያለው ቁልፍ ሚና በተገቢ ያላጤነና ኤርትራ እንድትገነጠል የተደረገበትን ሁኔታ የዘነጋ ይመስለኛል፡፡ በተጨማሪም መጀመሪያውኑም ስድሣ ዓመታት በባዕዳን ቅኝ ግዛት ሥር የቆየው የኤርትራ ሕዝብ “እንደፈለገው ይሁን” ተብሎ ችላ ሊባልና ተመልሶ ከቀረው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር እንዲቀላቀል በኤርትራውያንና በኢትዮጵያውያን በኩል የተደረገው መራር ትግል አግባብም ሆነ አስፈላጊነት አልነበረውም እንደ-ማለት ይሆናል፡፡

ሌሎች ደግሞ "ስምምነት" የሚለው ጉዳይ ከመንግሥት መንግሥትና ሥልጣን እንደያዙት ሰዎች አመኔታና የየወቅቱ ሁኔታ ስለሚቀያየርና አስተማማኝነት ስለማይኖረው ኢትዮጵያ አሰብን በቀጥታ ባለቤትነት ልትቆጣጠር ይገባል ይላሉ፡፡ ይኸንን አሣብ አንዳንዶች ከኤርትራ ጋር የሚያጋጭ ነው ሲሉ፣ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎችና የፖለቲካ ደቀ-መዝሙሮቻቸው ደግሞ "*የሌላ አገርን ሉዓላዊነት መድፈር ስለሚሆን በዓለም ፊት ያስጠይቃል*፣.. አለፍ ብለውም "*ጨርሶ የማይታሰብ ነው*" ይላሉ፡፡ ምክንያታቸውም "*ኢትዮጵያ ከውጭው ዓለም ጋር የንግድ ልውውጥ ማድረግ የሚያስችላት* ***የወደብ አገልግሎት*** *እስካገኘች ድረስ* ***የራሷ የሆነና በባለቤትነት በቀጥታ የምትቆጣጠረው*** *የባሕር በር አያስፈልጋትም*" በሚል ምናልባትም '*ብሔራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ ንግድ እንጂ መሬት መያዝ አያስፈልግም* – Commerce Not Territory' ከሚለው የካፒታሊስት የእጅ አዙር የቅኝ ገዥ ሥነ-ልቦናና ስሌት አኳያ በተቃኘ አስተሣሰብ የባለቤትነትን ጥያቄ በጭንቅላቱ በቆመ ሥነ-አመክኖ ሲያጣጥሉት ይሰማሉ፡፡

በእርግጥ ኤርትራ ከሕዝቧ ቀጥሎ ያላት ትልቅ ጥሪት የቀይ ባሕር ወደቦች እንደሆኑ ግልጥ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሕዝቡን አፍኖ ከያዘው የኢሣኢያስ አፈወርቂ ፍፁም አምባገነን የአገዛዝ ሥርዓት ውጭ የኤርትራ መሠረታዊ የሆነ ትልቁ ችግር አገር መሆን የመቻል ጉዳይ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ኤርትራ የዛሬ ሃያ ዓመት በነአቶ መለስ ጥብቅናና ዋቢነት ከኢትዮጵያ ተገንጥላ የራሷ መንግሥት ከመመሥረቷ በፊት አንድም ጊዜ አሁን የያዘችውን ቅርፅ ይዛ እራሷን የቻለች ነፃ አገር የሆነችበት ጊዜ አልነበረም፡፡ በበላይነት ቅኝ የገዟት ባዕዳን ኤርትራን "ለማስተዳደር" ከየመንግሥታቸው ግምጃ-ቤት (ካዝና) የድጎማ ወጭ እያደረጉ እንደቆዩ ይታወቃል፡፡ በኢትዮጵያ አቅም እንኳ ኤርትራን ለመደጎም በዓመት እስከ ሦስት መቶ ሚሊዮን ብር ወጭ ታደርግ እንደ-ነበር ይታወቃል፡፡

ለኤርትራ አገር ሆኖ በእግር ለመቆም ያለው ችግር ከኤኮኖሚው ጎን ብቻ የሚታይ አይደለም፡፡ ከአጠቃላዩ የምጣኔ ሃብት ውሱንነት ይበልጥ ለኤርትራ እንደ አገር የመቀጠል ፈተና የሚመነጨው በአሁኑ ጊዜ በኢሣኢያስ አፈወርቂ የሽዓብያ የአፈና መረብ ተወጥሮ የተያዘና ሊፈነዳ የደረሰ የውስጥ ሁኔታና በተለይም አክራሪነትና ታጣቂነት እየተበራከተ በመጣበት ዓለም ክፍል መገኘቷ ይሆናል፡፡ በዚኽ የውጭ ኃይሎችን ትኩረት እየሣበ በመጣ የአፍሪቃ ቀንድ የምትገኘዋ ኤርትራ ማንነቷን ጠብቆ ለማቆየት የግድ መረጋገጥ ካለበት የፀጥታ ሁኔታና ኤርትራ አሁን ባለችበት ደረጃ ያንን ማድረግ ካላት አቅም አኳያ ሊታይ ይገባል፡፡ በዚኽ ረገድ የባሕር ጠረፏ ቁልፍ ሚና እንዳለውና በአንድ በኩል በአክራሪዎች፣ በሌላ በኩል በጥሬ ሃብት ተቀራማቾች መኻል በሚኖር ሽኩቻ የመፋለሚያ መድረክ ከመሆን አኳያም ሊማዘን ይገባል፡፡ ስለ-ሆነም በዚኽ ኤርትራን አገር አድርጎ በማቆም ረገድ ቀድሚያ ከሚጠቀሰው ታላቁና ታታሪው ሕዝቧ ጎን-ለጎን የሕዝቡን በእርግጥ ነፃ መሆን፣ ሰላምና መረጋጋትን የሚጠይቀውና ወሣኝ ድርሻ ያለውን ፀጥታ በአስተማማኝ መከበርና መረጋገጥ የግድ ይሆናል፡፡ እነዚኽ እሴቶች ደግሞ እውን በመሆንና ባለ-መሆናቸው ላይ የባሕር ወደቦቻቸው በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋል አለመዋላቸውና ከዚሁ ጋር የተጎዳኙ ጉዳዮች ወሳኝ ሚና ይኖራቸዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በኤርትራ ሙሉ ቁጥጥር ሥር በሚገኘው የቀይ ባሕር ጠረፍ ላይ ያሉትን ወደቦች (ምፅዋና አሰብን) አሻሽሎ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በኢትዮጵያ መንግስት (የአፄ ኃይለ-ሥላሴም ይሁን የደርግ) በኩል ምን ያኽል የአገሪቱ ጥሪት እንደፈሰሰና እንደ-ተደከመ ይታወቃል፡፡ ያ ደግሞ ከሕዝብ ጉሮሮ ተነጥቆ እንደሆነ ልብ ይሏል፡፡

እነኝኽ ወደቦች ጠቀሜታ የሚኖራቸው አገልግሎት ላይ ሲውሉ ነው፡፡ ወደቦቹን ደግሞ የኤርትራን ሕዝብ ክብርና ማንነት በማይነካ፣ ያለ ጫናና ተፅዕኖ ኤርትራውያን ከወደቦቻቸው ሊጠቀሙ የሚችሉት ሰማንያ ሰባት ሚሊዮን ቁጥር ያለው ወገናቸው የኢትዮጵያያ ሕዝብ ሊገለገልባቸው ሲችል ነው፡፡ ያም ስለ-ሆነ ነው አንዳንድ ወገኖች "*ቢያንስ የአሰብን ወደብ ኢትዮጵያ በባለቤትነት ከተቆጣጠረች ኢትዮጵያ ወደቦቹን በመገልገል ኤርትራ ልታገኝ የምትችለውን እንዳታገኝ ያደርጋል፤ ያ ሲሆን ደግሞ ኤርትራ ትጎዳለች፣ ትዳከማለችም*" የሚል ክርክር የሚያነሱት፡፡ ነጥቡ ከበጎ አመለካከት የመነጨ ነው፡፡ ሆኖም በእኔ አመለካከት ያ ክርክር እርቀት አይወስድም፡፡ ለምን ቢባል፤ ለምሣሌ

ጉዳዩን ጠበብ እናድርገውና ኢትዮጵያ የአሰብን ወደብ መልሣ በባለቤትነት ብትቆጣጠር ለኤርትራ ሦስት ተደጋጋፊ ግዙፍ ጥቅሞች ስለሚያስገኝላት ነው።

አንደኛ፣ ግልጥ የሆነውና የማይውል የማያድር ኤኮኖሚያዊ ጥቅም ነው። ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትለይ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ወደቦቹ ሊሰጡ በሚችሉበት ሙሉ አገልግሎት ላይ እንዳልሆኑና ያም በመሆኑ የኤርትራ ሕዝብ ሊያገኝ የሚገባውን ገቢና አጠቃላይ ጥቅም እንዳላገኘ ግልጥ ነው። ኢትዮጵያ የአሰብ ወደብን በባለቤትነት ብትቆጣጠርም እንኳ በዚኽ አንድ ወደብ አገልግሎት ብቻ እያደገ የሚመጣውን ሕዝብ የፍጆታ ፍላጎት ማርካት ስለማትችል ተጨማሪ የወደብ አገልግሎት እንደሚያስፈልጋት አጠያያቂ አይደለም። ስለ-ሆነም ያ ተጨማሪ ወደብ ፖርት-ሱዳን፣ ሞምባሣ ወይም ሌላ ከሚሆን ምፅዋ መሆኑ ተፈላጊ ይሆናል። በዚኽ መልክ አሁን ከሞላ-ጎደል ሥራ ፈትቶ የተቀመጠው የምፅዋ ወደብ ኢትዮጵያ በስምምነትና በውል ኢትዮጵያ እንድትገለገልበት ቢደረግ ለኤርትራ አስተማማኝ ገቢ ማስገኘትና ከዚሁም ጋር ተያይዘው የሚመጡ ጥቅሞችን ያስገኛል።

ሁለተኛ፤ የሕዝብን ሉዓላዊነትና ክብርን ከማስጠበቅና ቀጣይ አደጋን ከማስወገድ አኳያ ይሆናል። የኤርትራ ወደቦች አሁን ባሉበት ሁኔታ ከሞላ-ጎደል ቦዝነው መቀጠል ጥቅመ-ቢስ ከመሆኑና ለኤርትራ ሕዝብም ትርፍ ሣያስገኙ መቀጠላቸው ስለማያዋጣ በሕዝብ ፈቃድና ይሁንታ የማይመሩ የሽዓብያ መሪዎች ወደቦቹን ለባዕዳን ጦር ሠፈር አገልግሎት ሣይቀር ሊያከራዩ የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ያ ደግሞ ኤርትራን በዓለም ፊት የተወገዘችና የተነጠለች አገር ሆና እንድትቀጥል ከማድረጉም በላይ የኤርትራን ሕዝብ ሉዓላዊነት በቀጥታ የሚጻፈር፣ ኤርትራንም ለዓለም-አቀፍ ውዝግብ የሚዳርግና ለፍልሚያ መድረክነት የሚያመቻች አደገኛ ሁኔታን የሚፈጥር ይሆናል። ስለ-ሆነም ወደቦቹን፣ ማለትም አሰብን በባለቤትነት ምፅዋን በኪራይ ውል፣ ኢትዮጵያ እንድትገለገልባቸው ቢደረግ ሁለቱንም አደጋዎች ማስወገድና አስተማማኝ ጥቅምንም የሚያስገኝ ከመሆኑ አኳያ ጠቀሜታው የላቀ ይሆናል።

ሦስተኛ፤ የፖለቲካና የደኅንነት ዋስትናን በተመለከተ ይሆናል። በሁለቱ ወንድማማች/እትማማች ሕዝብ መኻል የወደብ ባለቤትነትና አጠቃቀም ከላይ በተጠቀሰው መልክ ማድረግ ከተቻለ በሁለቱም በኩል ያለው ያላስፈላጊ የውጥረት ሁኔታ እንዲወገድና አንዱ ሌላውን ለመተናኮልና ዕድገቱንና ሰላሙን ለማደናቀፍ የሚያደርገውን ከንቱ ድካምና ወጪ ሊያስቀር፣ የተበጣጠሱ ማኅበረሰባዊ የትሥሥር ገመዶች እንዲቀጠሉና ቁስሎች እንዲሽሩ፣ ቀስ በቀስም መተማመን እንዲዳብር ዕድል ሊፈጥር፤ ከስሜታዊነት በወጣ መልክ ዘለቄታዊ ጥቅሞችን ተረጋግቶ ለማሰብ ፋታ ሊሰጥ ይችላል። ይኽ ለጊዜው የጋራ ኤኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ የሚደረግ ጥረትም የወደፊት ግንኙነቶች ከኤኮኖሚው ውጭ ባሉት መስኮች ሁሉ እንዲሠፉ ስለሚያስችል፣ ሁለቱም ታሪክ ካቆራኛቸው አንድነት ውጭ ተለያይቶ መኖሩ ከጥቅሙ ጉዳቱ መብለጡን እንዲረዱና በስምምነትና በመግባባት አዲስ የትሥሥር ምዕራፍ እንዲጀምሩ ዕድል ይሰጣቸዋል።

ውጥረት ረግቦ ሰላምና መረጋጋት ሲሰፍን፣ በሁለቱም በኩል ያሉት ዜጎች የችግሮች ሁሉ መፍትኄ ከጠመንጃ አፈ-ሙዝ ብቻ የሚገኝ ከሚመስላቸው አፋኝ አምባ-ገነንና ጦርነት አቀንቃኝ ገዥዎች ተላቅቀው የወደፊት ዕድላቸውን መወሰን የሚያስችል የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት እንዲሆኑ የተሻለ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል። ያ ሲሆን ደግሞ የኤርትራ ሕዝብ ከወገኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በሰላም የመኖር ዕድልን የሚያስገኝለት ብቻ ሣይሆን የአፍሪቃ-ቀንድም ሆነ የቀረው የአፍሪቃ ሕዝብ በሰላምና በዴሞክራሲ መንገድ እንዲጓዝ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው መተንበይ ከባድ አይሆንም።

አሁን ያለው የማያዛልቅ ተፋጥጦ የመኖር የውጥረት ይዞታ በሁለቱም በኩል ላሉ አምባ-ገነኖች ዕድሜ መራዘም ከመጥቀም ውጭ ከሁለት ለተከፈለው ሕዝብ አንዳችም ጠቀሜታ የለውም። ያም ስለ-ሆነ ነው በወደብ ዙሪያ አዲስ የመፍትኄ አሣብ እንዲሰማ የማይፈልጉት። ውጥረት ከሌለና ሕዝብ በሰላም ከኖረ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን ይጠይቃል። ያ ደግሞ የአምባ-ገነኖቹ ፍጻሜ ይሆናል። ስለ-ሆነም ነው በሰላም ይሁን በብሔራዊ ክብር ስም ያለው የተፋጠጠ ሁኔታ እንዲቀጥል የሚፈልጉት።

***በክፍል አራት ይቀጥላል ....***